የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፶፭
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፯ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 55
ADDIS ABABA 24th July, 2014

ማውጫ

CONTENTS

ደንብ ቁጥር ፫፻፲/፪ሺ፮ ዓ.ም

የኢትዮጵያ የክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ................ገጽ ፯ሺ፬፻፷፭

Regulation No. 310/2014

Ethiopian Toll Roads Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation.................................... Page 7465

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፲/፪ሺ፮

## የኢትዮጵያ የክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯ (፩) (ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፲/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **መቋቋም**

፩/ የኢትዮጵያ የክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝ (ከዚህ በኋላ "ኢንተርፕራይዝ" የተባለ የሚጠራ) የመንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION NO. 310/2014

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN TOLL ROADS ENTERPRISE

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 47 (1) (a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Toll Roads Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation No. 310/2014".

2. **Establishment**

1/ The Ethiopian Toll Roads Enterprise (hereinafter the "Enterprise") is hereby established as a public enterprise.

www.chilot.me

፪/ ኢንተርፕራይዙ በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል፡፡

## ፫. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን

የትራንስፖርት ሚኒስቴር የኢንተርፕራይዙ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

## ፬. ዋና መስሪያ ቤት

የኢንተርፕራይዙ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

## ፭. ዓላማ

ኢንተርፕራይዙ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩/ ለመንገድ ተጠቃሚዎች የክፍያ መንገዶች አገልግሎት የመስጠት፣

፪/ የክፍያ መንገዶችን የማስተዳደርና የማስጠገን፣

፫/ በክፍያ መንገዶች ክልል ውስጥ የተሰሩ የአገልግሎት መስጫ ጣቢያዎችን የማስተዳደር፣

፬/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎች ማካሄድ፡፡

## ፮. ካፒታል

ለኢንተርፕራይዙ የተፈቀደለት ካፒታል ብር ፪፻፪ ሚሊዮን ፬፻፩ ሺህ ፰፻፵፫ (ሁለት መቶ ሁለት ሚሊዮን አራት መቶ አንድ ሺህ ስምንት መቶ አርባ ሶስት ብር) ሲሆን በጥሬ ገንዘብና በአይነት በሙሉ ተከፍሏል፡፡

## ፯. የኃላፊነት ወሰን

ኢንተርፕራይዙ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

2/ The Enterprise shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

## 3. Supervising Authority

The Ministry of Transport shall be the supervising authority of the Enterprise.

## 4. Head Office

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

## 5. Objectives

The objectives for which the Enterprise is established are:

1/ to provide toll road services to road users;

2/ to operate and ensure the maintenance of toll roads;

3/ to operate service stations constructed within the boundaries of toll roads;

4/ to undertake other related activities necessary for the attainment of its objectives.

## 6. Capital

The authorized capital of the Enterprise is Birr 202,401,843.00 (Two Hundred Two Million Four Hundred One Thousand Eight Hundred Forty Three Birr) which is fully paid up in cash and in kind.

## 7. Liability

The Enterprise shall not be liable beyond its total assets.

www.chilot.me

፰. **ኢንተርፕራይዙ የሚቆይበት ጊዜ**

ኢንተርፕራይዙ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል።

፱. **የተሻሩ ሕጎች**

በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፵፯/፪ሺ፫ አንቀጽ ፮ (፳፫) ላይ "ከተጠቃሚዎች የሚሰበሰብ የአገልግሎት ክፍያን ይሰበስባል፤ ለመንገድ ፈንድ ገቢ ያደርጋል" የሚለው ሐረግ በዚህ ደንብ ተሠርዟል።

፲. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፯ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

8. **Duration of the Enterprise**

The Enterprise is established for an indefinite duration.

9. **Repealed Laws**

The phrase "collect the toll road user fee and transfer the collected amount to the Road Fund" appearing in Article 6 (23) of the Ethiopian Roads Authority Re-establishment Council of Ministers Regulations No. 247/2011 is hereby deleted.

10. **Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 24th day of July, 2014.**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

www.chilot.me